# ማጣፊያው ታጠፈ

ተፈጥሮ ስትቀጣው ፣ ለቅሶውን አልቅሶ
ሲራብ እያበላ ፣ ከሚጎርሰው ቆርሶ
ትርፍ እንኳን ሳይኖረው ፣ ሲታረዝ አልብሶ
ደግፎ ያቆመውን ፣ ዋልታና ምሰሶ
ያዘለው ትከሻን ፣ ዘንግቶት ጨርሶ
ያጎረሰውን እጅ ፣ ግጥም አርጎ ነክሶ
መኖሪያ ጎጆውን ፣ ድንበሩን አፍርሶ
በግፍ እያረደው ፣ ደሙንም አፍስሶ
አገር ቀናች ይላል ፣ ይታበያል ደርሶ ።

ሳይተኛ የሚያድር ፣ ሴራ እንደዶለተ
ተሳቆ የሚኖር ፣ ሁለ እንደባተተ
ሜዳን ገደል የሚል ፣ አቅጣጫ የሳተ
አይምሮው ጨቅይቶ ፣ ሻግቶ የመረተ
ፍርሃት ያሳበደው ፣ በቁሙ የሞተ
በገዛ ፍቃዱ ፣ ካልተሰናበተ
መረገጥ ነው ምሱ ፣ እየተጎተተ ።

ገሎ አይገል በሽታ ፣ አብሯቸው የኖረ
በካንሰር ደረጃ ፣ ሁሉን የወረረ
አከመውት አይድን ፣ ፈታኝ ያስቸገረ
ሃብትና ስልጣኑን ፣ ቢገኝም ያልሻረ
ያገግማል ሲባል ፣ ዘመን አስቆጠረ
መቼም ፈውስ የለውም ፣ ገሎ ካልቀበረ ።

በምንም ከማንም ፣ አንሳለሁኝ ብሎ
እራሱን ዝቅ አርጎ ፣ ልቡ ተቀብሎ
አብሮት ያደገውን ፣ ከውስጡ ተተክሎ
አሁን በለጥኩ ቢል ፣ እራሱን አታሎ
ውስጡ አልተለወጠም ፣ ባፉም ተቆልሎ
እምነት መች ይጠፋል ፣ በቀላል ተነቅሎ
ዝቅተኛው ስሜት ፣ ካላጠፋው ገድሎ ።

ያናሳነት ደዌ ፣ ውስጡ የገዘፈ
ዜጋን ያረከሰ ፣ ትውልድ የጠለፈ
ጥላቻ ነግሶበት ፣ ጨቅይቶ ያደፈ
ዘመን የማይሽረው ፣ በቀል ያተረፈ
እከክ ስናስታምም ፣ ዓመታት አለፈ
የገላ እከክ ቢሆን ፣ ቀድሞ በረገፈ
ያንጎል እከክ ሆኖ ፣ ማጣፊያው ታጠፈ ።

ታዛቢው

May 4, 2018